# መለኮታዊ እይታ

ዘፍ 13-14 "... ዓይንህን አንሳና አንተ ካለህበት ስፍራ ወደ ሰሜን ደቡብ ወደ ምስራቅና ወደ ምዕራብ እይ የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጣለሁና፡፡

በእግዚአብሄር መለኮታዊ ጥሪ ከሀገሩና ከዘመዱ ተለይቶ የወጣው አብርሃም የሚወርሰው የምድር ስፋት የሚለካው "ባየው" ልክ ነበር፡፡ አብርሃም ትወርሳለህ የተባለው አንድ ጂኦግራፊካዊ ምድር ብቻ ነበር፡፡

በአዲስ ኪዳን የሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች ለሆነው ለእኛ ግን አሁን የሚሰጠን ጂኦግራፊካዊ ምድር ወይም አንድ የመሬት ርስት ሳይሆን ነገር ግን የሚሰጠን ወይንም ልንወርሰው ያለ ርስት ጌታ በመስቀሉ አማካኝነት ያስገኘልንን በዚህም ቁሳዊ አለም ሊገለጡ የሚችሉት መንፈሳዊ ርስቶችን ነው፡፡

የእነዚን መንፈሳዊ ርስቶች የሚገኙበትና የሚወርሱበት ብቸኛ መንገድ የልቦናችን ዓይኖች ሲበሩና በእምነት ዓይን ሲታዩ ነው፡፡

በክርስቶስ የመስቀሉ ስራ (በሞቱና በትንሳኤው) የተገኙት እነዚህ መንፈሳዊ በረከቶች በልቦናው ዓይኑ ያየ ይወርሳቸዋል፡፡

በመፅሐፍ ቅዱስ የመውረስ ህግ አለ፡፡ ያም "አምነህ ብታይ" የሚል ህግ ነው፡፡ ኤልሳ ሁለት እጥፍ ቅባት ያገኝ ዘንድ በትጋት የኤልያስን እንቅስቃሴ ማየት ነበረበት፡፡ ኤልያስ አለው "ብታይ" ይሆንልሀል አለው፡፡ (2 ነገስት 2፤10)

ለአብርሃም የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተ እሰጣለሁ ተባለ፡፡ በሌላ አባባል አበረሃም ሊወርሰው የሚችለው ባየው ልክ ወይንም የአብርሃም የርስት ስፋት ያየውን ያህል ነው፡፡

ለምሳሌ እኛ የዘላለም ሕይወት ያገኘነውና የዳንነው ስለ ደህንነት በቃሉ አማካኝነት በውስጣችን ስለበራልንና ውስጣዊ ዓይናችን ይህንን እውነት ከቃሉ ስለተመለከተ ነው፡፡

ስለ ደህንነት በውስጥ ዓይናችን ያን መረዳት ባናይ ዛሬ ባልዳዳን ነበር፡፡ ልክ እንደዚሁ በቃሉ አማካኝነት የሕሊናችን ወይም የልቦናችን ዓይኖች ሲበሩ ሌሎች መንፈሳዊ ርስቶችን ከቃሉ እንወርሳለን፡፡


www.Ethiocross.com

ለምሳሌ፡- በጌታ ስለተሰጠን ሰላም ሲበራልን ከፍርሃት ነፃ እንወጣለን፡፡ እንደዚሁም በመዝሙር 91 ያሉ የቃሉ እውነቶች በእምነት ከውስጥ ሰውነታችን ጋር ስናዋህደው ስጋት ከህይወታችን ይገፈፋል፡፡ ምክኒያቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ "እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል" (ዮሐ 8፤32)

ጌታ በምድር በነበረበት ዘመን የነበሩት የፈሪሳዊያን ችግራቸው ጌታን በእምነት ዓይናቸው አለማየታቸው ነበር (ዮሐ 9፤39-41)

ዛሬም ጌታ የውስጥ ዓይናችንን በከፈተው ቁጥር ከቃሉ የምንወርሳቸው ብዙ ርስቶች አሉ፡፡ ልክ አብርሃም "በምድሪቱ በርዝመቷ ተመላለሰ" እንደተባለ በቃሉ ምድር ላይ ተነስተን በርዝመቱ በቁመቱ ስንመላለስ በሌላ አባባል በመረዳት ባለጠግነት ስንሞላ (ቆላስያስ 2፤2-3 2ኛ ጴጥ 3፤18) ከጌታ ብዙ ርስቶችን እንወርሳለን፡፡ በቃሉ ውስጥ ብዙ መንፈዊ ርስቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የመለኮታዊ ሰላም ርስት ፤ የመለኮታዊ ጤንነት ርስት ፤ የመለኮታዊ ብልጽግና ርስት ፤ የመለኮታዊ ጥበቃ ርስት ፤ የመለኮታዊ መከናወን ርስት ፤ የመለኮታዊ ሞገስ ርስትና ሌሎች ርስቶችን ከቃሉ ዓይተን ስንወርሳቸው በሕይወታችን ላይ ይንፀባረቃሉ፡፡

ቃሉን የጌታ መንፈስ ሲያበራልን ያኔ በውስጣችን የበራው የቃሉ ፍቺ ያለማወቅን ጨለማ ይገፋል፡፡ "የቃልህ ፍቺ የበራል" (መዝ 119፤130)

የውስጥ ዓይናችን ጤናማ የሚሆኑት የቃሉን ዕውነት በሙላት ሲመለከቱ ነው፡፡ ያኔ የጨለማ ቁራጭ በኑሮአችን በሕይወታችን በቤታችን አይኖርም፡፡ ያ ያላየነው እንደዚሁም ያላወቅነው ነገር ያ ለእኛ የጨለማ ቁራጭ ነው፡፡

ለምሳሌ ስለመፈወስ እውነት በሙላት የቃሉ መረዳት ከሌለን በሽታ የጨለማ ቁራጭ ሆኖ ያስቸግረናል፡፡ ስለሌሎችም መንፈሳዊ እውነቶች እስካላወቅናቸው ድረስ በዚያ ባላወቅነው አቅጣጫ የጨለማ ቁራጭ አለ ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነው ጌታ እንዲህ ብሎ በ (ሉቃስ 11፤34-36) የተናገረው

የሰውነትህ መብራት ዓይንህ ናት፡፡ ዓይንህ ጤናማ በሆነች ጊዜ ሰውነትህ ሁሉ ደግሞ ብሩህ ይሆናል ፡፡ ዓይንህ ታማሚ በሆነች ጊዜ ግን ሰውነትህ ደግሞ የጨለመ ይሆናል፡፡ እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ተመልከት፡፡ እንግዲህ ሰውነትህ ሁሉ የጨለማ ቁራጭ የሌለበት ብሩህ ቢሆን መብራት በደመቀ ብርሃን እንደሚያበራልህ በጭራሽ ብሩህ ይሆናል (ሉቃስ 11፤34-36)



www.Ethiocross.com

የጨለማ ቁራጭ በህይወታችን የማይኖረው ወይንም የጠላት ተጽኖ በህይወታችን የማይኖረው ፍጹም ሙሉ በሙሉ የልቦናችን ዓይኖች ተከፍተው የጌታን የማዳኑን ስራን በእምነት ስንቀበልና እደዚሁም ክርስቶስ ከሞት በመነሳቱ የተረጋገጠልንን ርስት ስናይ ነው "ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሳቱ ሁሉን አረጋግጦአል" (ሐዋ 17፤31)

ጌታ ከሞት በመነሳቱ ማናቸውም መንፈሳዊና ሰማያዊ በረከቶች እርግጠኝነትን አግኝተዋል። እግዚአብሔር አብ ክርስቶስን ከሞት በማስነሳቱ ለእኛ ርስታችንን አረጋግጦልናል።

በጌታ መነሳት የተረጋገጠልን መንፈሳዊ ርስቶችን እንወርስ ዘንድ የልቦናችን ዓይኖች ሊበሩ ይገባል (ኤፌሶን 1:17-19)

የብሉይ ኪዳን መዝሙረኛ እንኳን ይህን በመረዳት እንዲህ አለ "ጠላቴ አሸነፍሁት እንዳይል የሚያሥጨንቁኝ እኔ ብናወጥ ደስ እንዳይላቸው ለሞትም እንዳልተኛ ዓይኖቼን አብራ" (መዝ 131፤9)

በኤፌሶን 6፤12 የተጠቀሱት ጠላቶች ሊያሸንፉህ የሚችሉትና በአንተም መናወጥ ደስ የሚላቸው የውስጥህ ዓይኖች ያንቀላፉ እለት ብቻ ነው። ስለዚህ ያ እንዳይሆን እንደ መዝሙረኛው ዘወትር ዓይኖቼን አብራ ጠላቴ እንዳያሸንፈኝ የቃልህን ፍቺ አብራልኝ ከህግህም ታምራት እንዳይ (መዝ 119፤18) ብለን ልንጸል ያስፈልጋል።

ዓይኖችህ በቃሉ ውስጥ ያዩትን የእውነት ልክ ያህል ነው ነፃነትህ! የነፃነትህ ልክ ያወቅከውን ወይንም የተረዳኸውን የእውነት ቃል ብዛት ያህል ነው! በውስጥህ እንዳለው የቃሉ ክምችት መጠን የህል የውጭውም ነፃነትህ የዚያኑ ያህል ነው! (ዮሐ 8፤32)

ጌታ የተመሰገነ ይሁን!

የውስጥ ዓይኖች የሚበሩት እኛ ስንጸልይ የጌታም መንፈስ ቃሉን ሲያበራልን ነውና ስለዚህ ከእግዚአብሔር የሆነ የማስተማር ቅባት ቃሉንም የመግለጥ ቅባት በቤተክርስቲያን ሊለቀቅ ይገባል። ያስተምሯቸው ዘንድ መልካሙን መንፈስ ሰጣቸው የተባለው ለዚህ ነው። እንደ እግዚአብሔር ቃል በሆነ ትምህርት ዓይን ይከፈታል ርስቱንም ማየት ያኔ ይቻላል።

በሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ ላይ በጥቂቱ ዓይኑ ተከፍቶለት በዚያ በተረዳው ጥቂት ብርሃን ሲተጋ የነበረው የአጵውሎስ ህየወት ልቤን ይነካዋል።

ያኔ ሰው ጥቂት ብርሃን ነበረው። በዚያ ብርሃን ሲተጋ ጌታ ጥማቱን አየና የውስጡ ዓይኖችን ሙሉ በሙሉ ከፈተለት። ጌታ የአጵውሎስን የመረዳት ባለጸግነት


www.Ethiocross.com

የጨመረለት እንደዚሁም እሱ ያላየውን ነገር ግን በጌታ ትንሳኤ የተረጋገጠውን ርስቱን ያሳየው በትምህርት ቅባት አማካኝነት ነበር፡፡

የአጵውሎስ ዓይኖች ከፊት ይልቅ በበለጠ ይበሩለት ዘንድ በዚህ የትምህርት ቅባት የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ወደ ሕይወቱ ላከለት፡፡ አጵውሎስም ትሁት ሰው ነበርና ዝቅ ብሎ ተማረ፡፡

እስቲ ታሪኩን ቀጥለን እንመልከት፡፡

በወገኑ የእስክንድሪያ ሰው የሆነ ነገር አዋቂ ነበር፡፡ አጵውሎስ የሚሉት አንድ አይሁዳዊ ሰው ወደ ኤፌሶን ወረደ፡፡ እርሱም በመጽሐፍ እውቀት የበረታ ነበር፡፡ እርሱም የጌታን መንገድ የተማረ ነበር፡፡ የዮሀንስን ጥምቀት ብቻ አውቆ በመንፈስ ሲቃጠል ስለ ኢየሱስ ይናገርና በትክክል ያስተምረ ነበር (ሐዋ 18፤24-25)

ይህ በመጽሐፍ እውቀት የበረታ የጌታን መንገድ የተማረ ስለ ጌታም የሚናገር ሰው ነበር፡፡ አጵሎስ ነገር ግን በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የተረጋገጡት እርሱ ግን ያላያቸው ሌሎች መንፈሳዊ እውነቶች ነበሩ፡፡ ስለዚህ ይሄ ሰው የበለጠ ዓይኑ ሊከፈትለት ይገባ ነበርና ጌታ ሰው ላከለት፡

“ጵርልቅልና አቂላም በሰሙ ጊዜ ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት” (26)

ገለጡለት የሚለውን ቃል አጵንኦት እንስጠውና ፡- ይህ ማለት አጵውሎስ ያልተገለጹለት እውነት ነበር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ የእግዚአብሔር ባሪያዎች የአጵውሎስን መረዳት ቃሉን ፍቺ በመግለጥ መረዳቱን ጨመሩለት፡፡ የውስጥ ዓይኖቹንም ከፈቱለት፡፡ የአጵውሎስም ዓይኖች ፈጽሞ ጤናማ ሆነው በሩ፡፡

ይሄ ሰው የመረዳቱን ሙላትና መገለጥን ያገኘው ከነዚህ ሰዎች ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ አጵምሎስ ቤተክርስቲያንን እጅግ የሚጠቅም ሰው ሆነ፡፡

“እርሱም ወደ አካይ ማለፍ በፈቀደ ገዜ ወንድሞቹ አጵናኑት ይቀበሉትም ዘንድ ወደ ደቀመዝራት ጻፉለት፡፡ በደረሰም ጊዜ <u>አምነው የነበሩትን በጸጋ እጅግ ይጠቅማቸው ነበር</u>፡፡” ቁጥር 27



www.Ethiocross.com

አጵውሎስ በትምህርት ቅባት ከተነካ በኂላ ቤተክርስቲያንን እጅግ የሚጠቅም ሰው ሆነ።

ዛሬም አኛን ጌታ በጥቂቱ ሳይሆን በብዙ የቃሉ እውነት ሊነካን ያስፈልገናል (ማር 8፤22-23) ያኔ በሚገባ በቃሉ እውነት ውስጣችንን ሲነካ አጥርተን ማየት እንችላለን። (ቁጥር 25)

ዛሬም አሁን ላለችው ቤተክርስቲያን የጌታን እውቀት በብዙ መረዳት የሚገልጹ ሰራተኞችን እንዲያስነሳል ልንፀልይ ይገባል። የነጰርቂላና አቂላ ቅባት በቤተክርስቲያን ሊለቀቅ ያስፈልጋል። ያን ጊዜ "በቅድሳት ዘንድ ያለውን የርስት ክብር ባለጠግነት" (ኤፌ 1፤19) ማየት እንችላለን። ከማየትም አልፈን በመውረስም ሌሎችን የምንጠቅም እንሆናለን።

የሌሎችን ዓይኖች በመክፈትም እንደ አጵውሎስ ቤተክርስቲያንን የሚጠቅሙ ሰዎች እንዲሆኑ ማድረግ እንችላለን።

ለዚህ የጠራን ጌታ ስሙ ይባረክ !!

ወንድም መላኩ አበጄ

MELAKU ABJE GOSHU

NEW COVENANT MINISTERY



www.Ethiocross.com